የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23nd Year No. 64
ADDIS ABABA, 14th July ,2017

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፬/፪ሺ፱ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በፍልስጤም መንግሥት መካከል የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ................................ገጽ ፱ሺ፯፻፮

## CONTENT

Proclamation No. 1034/2017

Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Palestine for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation ………………Page 9706

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፬/፪ሺ፱

## በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈጸምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በፍልስጤም መንግሥት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በፍልስጤም መንግሥት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈጸምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

PROCLAMATION No. 1034/2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CONVENTION BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE STATE OF PALESTINE FOR THEAVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OFFISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME

**WHEREAS**, a Convention for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income (the Convention) was signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Government of the State of Palestine on the 9th of July 2015, in Addis Ababa;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said convention at its session held on 29th June,2017;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia , it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ይህ አዋጅ "በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር ... ደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በፍልስጤም መንግሥት መካከል የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፬/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በፍልስጤም መንግሥት መካከል ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈጸምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Palestine for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No. 1034/2017".

**2. <u>Ratification of the Convention</u>**

The Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Palestine for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed on the 9th of July 2015 is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to implement the Convention in cooperation with the concerned government organs.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of July, 2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**